ደብረ - ታቦር ዩኒቨርሲቲ
Debre Tabor University
Debre Tabor University has a Historical duty to answer Tewodros's quest for knowledge

ትምህርተ ግእዝ

በተመስገን አዱኛው

ልጆቹ ኢያለን ግእዝ

ኢይሞትም

ደብረ-ታቦር ዩኒቨርሲቲ

Debre Tabor University

Debre Tabor University has a Historical duty to answer Tewodros's quest for knowledge

የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ግእዝን
ለመታደግ ከነሃርቫርድ ጎን ይሰለፋል
የሚል ታሪካዊ ተስፋ እንጥልበታለን

ግእዝ

የራሱ ፊደልና አሐዝ ያለው ብቸኛው የጥቁር ህዝብ ቋንቋ

ግእዝ

ጥበብ የተጻፈበት የጠበብት ቋንቋ

- የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ግእዝን በማስተማር የብራናውን እውቀታችን ወደ ተግባር ቢቀይረው የሚል ህልም አለን

ግእዝ

አፍሪካዊ ከጥፋት ሊታደገው የሚገባ

ፊደላተ ልሳነ ግእዝ
የግእዝ ቋንቋ ፊደላት

- ፊደል ብሂል ምንት ብሂል ውእቱ □
- ፊደል ማለት ምን ማለት ነው □

ፊደለ □ ቀ □□ ጻፈ □ .....ፊደል

እስፍንት ፊደላት ቦቱ ልሳነ ግእዝ □

=የግእዝ ቋንቋ ስንት ፊደላት አሉት □

26 □ 7 □ =182 4 □ 5 □ =20 182+20=202

በቀይ የተጻፉት የግእዝ ፊደላት ያልሆኑ ናቸው

ሀ	በ	ወ	ጨ
ለ	ተ	ዐ	ጰ
ሐ	ቸ	ዘ	ጸ
መ	ነ	ዠ	ፀ
ሠ	ኘ	የ	ፈ
ረ	ኀ	ደ	ፐ
ሰ	አ	ጀ	ቨ
ሸ	ከ	ገ	
ቀ	ኸ	ጠ	

አማርኛ አዲሶችን ሆሂያት እንዴት እንደተጠቀመ

- እድ=እጅ
- ሲበት=ሺበት
- ስንት=ሽንት
- ምሴት=ምሽት
- ሲመት=ሹመት

ኰ ኲ ኵ ኳ ኴ

ኈ ኊ ኍ ኋ ኌ

ጐ ጒ ጕ ጓ ጔ

ቈ ቊ ቍ ቋ ቌ

ሞክሼ ሆሄያት ና አገልግሎታቸው

- ✔ሀ=ሃሌታው
- ✔ሰ =እሳቱ
- ✔ አ=አልፋው/አሌፉ
- ✔ጸ=ጸሎቱ
- ✔ሐ=ሐመሩ
- ✔ሠ=ንጉሡ
- ✔ ዐ =አይኑ
- ✔ፀ= ፀሐዩ
- ✔ኀ=ብዙኀን

- ✔መሀረ =አስተማረ
- ✔ ሰብሀ=አመሰገነ
- ✔አመት=አገልጋይ □ ወ □
- ✔ ፈጸመ
- ✔መሐረ=ይቅር አለ
- ✔ሠብሀ=ወፈረ
- ✔ዓመት=365 ቀን
- ✔ ፈፀመ □ ግ □
- ✔ሐለየ=አሰበ
- ✔ኃለየ=ዘመረ

አኃዛተ ልሳነ ግእዝ

- አኃዘ=ቆጠረ
- አኃዝ=ቁጥር

- ፩ = አሃዱ
- ፪ = ክልኤቱ
- ፫ = ሠለስቱ
- ፬ = አርባዕቱ
- ፭ = ኀምስቱ
- ፮ = ስድስቱ
- ፯ = ሰብዓቱ
- ፰ = ሰምንቱ
- ፱ = ተስዐቱ
- ፲ = ዐሠርቱ

፲፩=አስርቱወአሃዱ

፲፱=አስርቱወተሳቱ

፳=እሥራ

፴=ሠላሳ

፵=አርባ

፶=ሃምሳ

፶=ሃምሳ

፷=ስሳ/ስድሳ

፸ =ሰብዓ

፹ =ሰማንያ

፺=ተስዓ

፻=ምዕት

፻ ፳ ፩=ምዕት እስራ ወአሐዱ

መራሕያን □ ተውላጠ ስሞች □

- መርሐ=መራ
- መራሒ=መሪ
- መራህያን=መሪወች
- የግእዝን ቋንቋ የሰዋሰው ስርዓት ይመራሉ

ሦስት መደቦች አሏቸው

- አንደኛ መደብ 2 አሉ
- ሁለተኛ መደብ 4 አሉ
- ሦስተኛ መደብም 4 አሉ
- 10

የቀጠለ...

- አንደኛ መደብ =ተናጋሪው ራሱን ሲጠቁም =እኔ፣እኛ
- ሁለተኛ መደብ= ተናጋሪው አድማጩን ሲጠቁም =አንተ፣አንቺ፣እናንተ
- ሦስተኛ መደብ=ተናጋሪው ስለሌላ ሰው ሲያወራ=እሱ፣እሷ፣እነርሱ
- በአማርኛ ጠቅላላ=8
- በግእዝ ግን=10

አንደኛ መደብ

- ✔ አነ
  =እኤ
- ✔ ንሕነ
  =እኛ

ሁለተኛ መደብ

- ✔አንተ
  =አንተ
- ✔አንቲ
  =አንቸ
- ✔አንትሙ
  =
  እናንተ□ወ□
- ✔አንትን
  =
  እናንተ□ሰ□

ሦስተኛ መደብ

- ይእቲ
  =እርሷ
- ውእቱ
  =እርሱ
- ውእቶሙ
  =እነርሱ □ ወ □
- ውእቶን
  =እነርሱ
  □ ሴ □

እንደመሆን ግስ ሲያገለግሉ

- በአማርኛ የመሆን ግሶች የምንላቸው

1 ነኝ፣ነበርኩ፣እሆናለው

2 ነን፣ነበርን፣እንሆናለን

3 ነህ፣ነበርህ፣ትሆናለህ

4 ነሽ፣ነበርሽ፣ትሆኛለሽ

5 ናችው፣ነበራችው፣ትሆናላችው

6 ነው፣ነበር፣ይሆናል

7 ናት፣ነበረች፣ትሆናለች

8 ናቸው ነበሩ ይሆናሉ

በግእዝ ግን ራሳቸው መራሕያን የመሆን ግሶች ናቸው

- ✔ አነ
  - = ነኝ፣ነበርኩ፣እሆናለው
- ✔ ንሕነ
  - = ነን፣ነበርን፣እንሆናለን
- ✔ አንተ
  - = ነህ፣ነበርህ፣ትሆናለህ
- ✔ አንቲ
  - = ነሽ፣ነበርሽ፣ትሆኛለሽ
- ✔ አንትሙ
  - = ናቹው፣ነበራቹው፣ትሆናላቹው

- ✔ አንትን
  - ＝ናችው፣ነበራችው፣ትሆናላችው
- ✔ ይእቲ
  - ＝ ናት፣ነበረች፣ትሆናለች
- ✔ ውእቱ
  - ＝ነው፣ነበር፣ይሆናል
- ✔ ውእቶሙ
  - ＝ናቸው፣ነበሩ፣ይሆናሉ
- ✔ ውእቶን
  - ＝ ናቸው፣ነበሩ፣ይሆናሉ ሴ

መራሕያን በስሞች ሲረቡ

- አነ=የ
- ንሕነ=ነ
- አንተ=ከ
- አንቲ=ኪ
- አንትሙ=ክሙ
- አንትን=ክን

- ውእቱ=ኡ □ ሳድስ □
  =ሁ □ ሌላ □
- ይእቲ=ኣ □ ሳድስ □
  =ሃ □ ሌላ □
- ውእቶሙ=ኦሙ □ ሳድስ □
  =ሆሙ □ ሌላ □

ውእቶን=ኦን □ ሳድስ □
=ሆን □ ሌላ □

ምሳሌ በሳድስ

- እም=እናት
- እምየ=እናቴ
- እምነ=እናታችን
- እምከ=እናትህ
- እምኪ=እናትሽ
- እምክሙ=እናታችው
- እምክን=እናታችው □ ሴ □

- እሙ=እናቱ
- እማ=እናቷ
- እሞሙ=እናታቸው
- እሞን=እናታቸው □ ሴ □

ምሳሌ በሌላ

- ሰሌዳየ＝ሰሌዳየ
- ሰሌዳነ＝ሰሌዳችን
- ሰሌዳከ＝ሰሌዳህ
- ሰሌዳኪ＝ሰሌዳሽ
- ሰሌዳክሙ＝ሰሌዳችው □ ወ □
- ሰሌዳክን＝ ሰሌዳችው □ ሴ □
- ሰሌዳሁ＝ሰሌዳው
- ሰሌዳሃ＝ሰሌዳዋ
- ሰሌዳሆሙ＝ሰሌዳቸው □ ወ □
- ሰሌዳሆን＝ሰሌዳቸው □ ሴ □

መራህያን በመስተዋድዶች ሲረቡ

የተለመዱ መስተዋድዶች

- እስከ=እስከነ=እስከ
- ቅድመ=ፊት/በፊት
- እም=እምነ=ከ
- መንገለ=ወደ
- መትህት=በታች
- ኀበ=ወደ
- እንበለ=ያለ
- ዲበ=በ ላይ
- ምስለ=ጋር

የመጨረሻውን ፊደል ወደ ኀምስ መለወጥና ከላይ ያየናቸውን ቅጥያወችን መጨመር

- እስከነ=እስከ
- እስከኔየ=እስከኔ
- እስከኔነ=እስከኛ
- እስከኔከ=እስከአንተ
- እስከኔኪ=እስከአንቺ
- እስከኔክሙ=እስከናንተ
- እስከኔክን=እስከእናንተ □ ሴ □
- እስከኔሁ=እስከእርሱ
- እስከኔሃ=እስከእርሷ
- እስከኔሆሙ=እስከእነርሱ
- እስከኔሆን=እስከእነርሱ □ ሴ □

መራህያን በግሦች ሲዘረዘሩ

- አንዳንድ ግሦች
- መሀረ=አስተማረ
- ወረደ=ወረደ
- ሰከበ=ተኛ
- ሰተየ=ጠጣ
- ቀደሰ=አመሰገነ
- ተፈስሀ=ተደሰተ
- ሐረ=ሄደ
- ሐተተ=መረመረ
- ሀከመ=አከመ

የግሱን የመጨረሻ ፊደል ወደ ሳድስ መቀየር ከይዕቲ ውጭ

- አነ ወረድኩ=እኔ ወረድኩ
- ንሕነ ወረድነ= ወረድን
- አንተ ወረድከ =ወረድክ
- አንቲ ወረድኪ =ወረድሽ
- አንትሙ ወረድክሙ =ወረዳችው
- አንትን ወረድክን =ወረዳችው □ ሴ □

- ውእቱ ወረደ =ወረደ
- ይእቲ ወረደት =ወረደች
- ውእቶሙ ወረዱ =ወረዱ
- ውእቶን ወረዳ =ወረዱ □ ሴ □

		ዝንቱ＝ይህ	ዝስኩ＝ያ ውእቱ＝ያ
	ሴት	ዛ＝ይህች ዛቲ＝ይህች	እንታክቲ＝ያች ይእቲ＝ያች
	ወንድ	እሉ＝እነዚህ ወ እሎንቱ＝እነዚህ	እሙንቱ＝እነዚ ውእቶሙ＝እነዘ
	ሴት	እላ＝እነዚህ ሴ	እማንቱ＝እነዚያ

ኪ.ያየ=ራሴን	ለሊ.የ=ራሴ	ዚ.አየ=የኔ
ኪ.ያነ=ራሳችንን	ለሊ.ነ=ራሳችን	ዚ.አነ=የኛ
ኪ.ያክ=ራስክን	ለሊ.ክ=ራስህ	ዚ.አክ=የአንተ
ኪ.ያኪ.=ራስሽን	ለሊ.ኪ.=ራስሽ	ዚ.አኪ.=የአንች
ኪ.ያክሙ=ራሳችውን	ለሊ.ክሙ=ራሳችው	ዚ.አክሙ=የናንተ
ኪ.ያክን=ራሳችውንሴ	ለሊ.ክን=ራሳችው	ዚ.አክን=የናንተ
ኪ.ያሁ =ራሱን	ለሊ.ሁ=ራሱ	ዚ.አሁ=የሱ
ኪ.ያሃ=ራሷን	ለሊ.ሃ=ራሷ	ዚ.አሃ=የሷ
ኪ.ያሆሙ=ራሳቸውን	ለሊ.ሆሙ=ራሳቸው	ዚ.አሆሙ=የነርሱ
ኪ.ያሆን=ራሳቸውን	ለሊ.ሆን=ራሳቸው	ዚ.አሆን=የነርሱ

- <u>መጠይቃዊ ቃላት</u>
- እፎ=እንዴት ፣ እፎ ሀምሰይከ=እንዴት አመሸህ □
- አይቴ=ወዴት/የት፣ አይቴ ትትዋነይ =የት ትጫወታለህ □
- ማዕዜ=መቼ፣ማዕዜ ትርዕይ ኳሄለ=ኳስ መቼ ታያለህ □
- ስፍን/እስፍንት=ስንት፣ እስፍንት ትሰትይ=ስንት ትጠጣለህ □
- ምንት=ምን፣ ምንት አእመርከ=ምን አወቅህ □
- ለምንት=ለምን፣ ለምንት ትነውም=ለምን ትተኛለህ □
- መኑ=ማን፣መኑ ውእቱ አማናዊ=እውነተኛ ማን ነው

የዝምድና ቃላት

- እኅ=ወንድም
- እኅት=እኅት
- እም=እናት
- አብ=አባት
- ሐው=ወንድ አያት
- ሐውት= ሴት አያት
- ወለት=ሴት ልጅ
- ወልድ=ወንድ ልጅ
- ዱድ=አጎት
- ዱዲት=አክስት
- ገብር=አገልጋይ ለወንድ
- አመት=አገልጋይ

የቦ እርባታ

- መደበኛ ሆነው ሲያገለግሉ
- ብየ= በእኔ፣አለኝ፣አለብኝ፣ኖረብኝ፣ነበረብኝ፣ነበርሁ፣አለሁ
- ብነ= በእኛ፣አለን፣አለብን፣ኖረብን፣ነበረብን፣ነበርን፣አለን

- ብከ= በአንተ፣አለህ፣አለብህ፣ዋረብህ፣ነበረብህ፣ነበርህ፣አለህ
- ብኪ= በአንቺ፣አለሽ፣አለብሽ፣ዋረብሽ፣ነበረብሽ፣ነበርሽ፣አለሽ
- ብክሙ= በእናንተ፣አላችሁ፣አለባችሁ፣ዋረባችሁ፣ነበረባችሁ፣ነበራችሁ፣አላችሁ
- ብክን= በእናንተ፣አላችሁ፣አለባችሁ፣ዋረባችሁ፣ነበረባችሁ፣ነበራችሁ፣አላችሁ

- ቦቱ= በእርሱ፣አለው፣አለበት፣ኖረበት፣ነበረበት፣ነበር፣አለ
- ባቲ= በእርሷ፣አላት፣አለባት፣ኖረባት፣ነበረባት፣ነበረች፣አለች
- ቦቶሙ/ቦሙ= በእነርሱ፣አላቸው፣አለባቸ፣ኖረባቸው፣ነበረባቸ፣ነበሩ፣አሉ
- ቦቶን/ቦን= በእነርሱ፣አላቸው፣አለባቸ፣ኖረባቸው፣ነበረባቸ፣ነበሩ፣አሉ

ተቀባይ ሆነው ሲያገለግሉ

ብየ

=ብኝ

ብነ

=ብን

ብከ

=ብህ

ብኪ

=ብሽ

ብክሙ

=ባቸው

ብክን

=ባቸው □ ሴ □

ቦቱ

=በት

ባቲ

=ባት

ቦቶሙ/ቦሙ

=ባቸው

ቦቶን/ቦን

=ባቸው □ሴ□

የለ እርባታ

- መደበኛ ሆነው ሲያገለግሉ
- ሊ.ተ/ልየ=ለእኔ፣አለኝ፣አለልኝ፣ዋረልኝ፣ነበረልኝ፣ይገባኛል
- ለነ=ለእኛ፣አለን፣አለልን፣ዋረልን፣ነበረልን፣ይገባናል

- ለከ= ለአንተ ፣አለህ፣አለልህ፣ኖረልህ፣ነበረልህ፣ይገባሃል
- ለኪ= ለአንቺ ፣አለሽ፣አለልሽ፣ኖረልሽ፣ነበረልሽ፣ይገባሻል
- ለክሙ= ለአናንተ ፣አላችሁ፣አለላችሁ፣ኖረላችሁ፣ነበረላችሁ፣ይገባችኋል
- ለክን= ለአናንተ ፣አላችሁ፣አለላችሁ፣ኖረላችሁ፣ነበረላችሁ፣ይገባችኋል

- ሎቱ= ለእርሱ፣አለው፣አለለት፣ኖረለት፣ነበረለት፣ይገባዋል
- ላቲ= ለእርሷ፣አላት፣አለላት፣ኖረላት፣ነበረላት፣ይገባታል
- ሎን/ሎቶን= ለእነርሱ፣አላቸው፣አለላቸው፣ኖረላቸው፣ነበረላቸው፣ይገባቸዋል
- ሎሙ/ሎቶሙ= ለእነርሱ፣አላቸው፣አለላቸው፣ኖረላቸው፣ነበረላቸው፣ይገባቸዋል

ተቀባይ ሆነው ሲያገለግሉ

ልየ/ሊተ

＝ልኝ

ለነ

＝ልን

ለከ

＝ልህ

ለኪ

＝ልሽ

ለክሙ

＝ላቸው

ለክን

＝ላቸው □ ሴ □

ሎቱ

=ለት

ላቲ

=ላት

ሎቶሙ/ሎሙ

=ላቸው

ሎቶን/ሎን

=ላቸው (ሴ)

ግሥ

- ጌሠ=ገሠሠ

የግስ ስልቶች

1 ገቢር፤ባለቤቱ ምን ሰራ □ አርጎወ=ከፈተ

2 ተገብሮ ፤ከገቢር ግሥ በፊት “ተ”ን በመጨመር የሚገኝ፤

□ በምን በምን ግዜ እንጠቀማለን □

በ“ተ” የጀመረ ሁሉ ተገብሮ ግስ ነው ወይ □

✔ተንበለ=ለመነ ✔ተሞገሰ=ባለሟል ሆነ

✔ተምዐ=ተቆጣ✔ተመነየ=ተመኘ

የቀጠለ...

3 ነባር አንቀጽ፣አደረገ ወይም ተደረገ የሚይሉ "መኖር/አለመኖር፣መሆን/አለመሆን"ን የሚገልጹ

- ✔ውእቱ=ነው፣ ነበረ፣አለ፣ ኖረ
- ✔ቦ= አለ፣ ኖረ፣ ነበረ
- ✔አኮ=አይደለም፣
- ✔አልቦ=የለም፣ አልኖረም፣ አልነበረም

ነባር አንቀጽ

ከዋና ግሦች ጋር

- የሚለዩበት
  - ከግእዝ ዉጭ መጨረሳቸው
  - በአንቀጽ አለመዘርዘራቸው
- የሚመሳሰሉበት
  - ማሰር መቻላቸው
  - በዐሥሩ መራሕያን መዘርዘር መቻላቸው

4 ግዑዝ ግሥ፦የማይሻገር ግስ ማን ተደረገ □ አይመልስም

ቅርጹ፦

ገቢር ግሥን ይመስላል

ቃላትን ባለመሳቡ □ ባለመሻገሩ □

ተገብሮ ግሥን ይመስላል

ምሳሌዎች

- ኖመ＝አንቀላፉ
- ሞተ＝ሞተ
- ቆመ＝ ቆመ
- ፆመ＝ፆመ
- ሀለወ＝ኖረ
- ሖረ＝ሄደ
- ኖመ＝ተኛ
- ደቀሰ＝ተኛ
- ሰከበ＝ተኛ
- ኀየ＝ሸሸ

ትውውቅ

ሀ፥ ሰላም ለከ (ሰላም ለአንተ ይሁን)

ለ፥ ወሰላም ለከ (ሰላም ላንተም)

ሀ፥ መኑ ስምከ?ስምህ ማን ነው?)

ለ፥ ቡሩክ ውእቱ ስምየ።(ስሜ ቡሩክ ነው።)

ሀ፥ ወመኑ ስመ አቡከ (የአባትህ ስም ማን ነው?)

ለ፥ ኖላዊ ውእቱ ስመ አቡየ(ያባቴ ስም ኖላዊ ነው።)

ሀ፥ እስፍንቱ አዝማኒከ? (እድሜህ ስንት ነው?)

ለ፥ እሥራ ወክልኤቱ (ሀያ ሁለት)

ትውውቅ

ሀ፥ እም አይቴ መጻእከ (ከየት መጣህ?)

ለ፥ እም አዲስ አበባ (ከአዲስ አበባ)

ሀ፥ ግብር እፎ ውእቱ (ሥራ እንዴት ነው?)

ለ፥ ሚመ ኢይብል (ምንም አይል)

ሀ፥ እሉ አብያጺከ ውእቶሙ (እነዚህ ጓደኞችህ ናቸው?)

ለ፥ እወ (አዎ)

ሀ፥ አይቴ ብሔሮሙ (ሀገራቸው የት ነው?)

ለ፥ ኤርትራ ወእቱ (ኤርትራ ነው።)

ሀ፥ አይቴ ውእቱ ቤተ ትምህርትከ (ትምህርት ቤትህ የት ነው?)

ለ፥ አድማስ ውእቱ ቤተ ትምህርትየ (አድማስ ነው ትምህርት ቤቴ።)

ሀ፥ በል እግዚእ የሀብከ ፀንአቶ ወይከስትለከ (በል ጌታ ፅናትን ይስጥህ ይግለፅልህም።)

ለ፥ አሜን (ይሁንልኝ /ይደረግልኝ)